የምኖርለት አለኝ

መኖርን ፈልግኩዋት
መኖርን ወደድኩዋት፡
ሁኜ ከየትም
በሃሳብም በስሜትም
ደግሞ ሁለት ሺዉ፡
ነፋሴ
ወንዜ
ህዝቤ
አገሬ አስባለኝ፡
እኔማ የምኖርለት አለኝ
ጤና ይስጠኝ!
እድሜ ይስጠኝ።

ሁለት ሺሕ ሲጠባ:

ሁለት ሺሕ ሲጠባ
አንቺ አዲስአበባ
እኔና አንቺ ብንጋባ
የመሰክርልናል ህዝቡ፡
በዝማሬዉ
በእልልታዉ
በሆታዉ
በእስክስታዉ፡
የፍቅራችንን ፅኑነቱ
የትዳራችንን ክቡርነቱ።
ሁለት ሺሕ ሲጠባ
አንቺ አዲስአበባ
እኔና አንቺ ብንጋባ
ሕዝቡ ነዉ ሰርገኛዉ
ሕዝቡ ነዉ እድምተኛዉ።



አንቺ አዲስአበባ
የሁለት ሺሕዋ
ፀሃይዋ
ብቅ ከማለትዋ፡
ፍቅር-ፍቅር አለኝ
እስቲ ፈካ በዪ
ፈገግታሽ ላኪልኝ፡
እንዉረሳት ደስታን
እንፍታዉ
ሚስጢሩን
የመፈጠራችንን።
አንቺ የኔ ሙሽራ
አንቺ አዲስ አበባ
እንዉረሳት ደስታን
እንፍታዉ
ሚስጢሩን
የመፈጠራችንን፡
ያቺ ፀሃይዋ
የሁለት ሺሕዋ
ብቅ ከማለትዋ።



አለሙ ይወቀዉ!

ስለ ተራሮቹ
ስለ ወንዞቻችን፡
ስለ መልካሙ ነፋስ
ስለ ፀዳላችን፡
ስለ ህዝቡ
ስለ ታሪካችን፡
ሁሌም ወሬ አለን።
ሁለት ሺሕ ስንልም
አልቆጠርንም ዘመን፡
ነዉ የተናገርነዉ ስለራሳችን
አለሙ ይወቀዉ እኛነታችንን።

፪ooo

የምኖርለት አለኝ

መኖርን ፈልግኩዋት
መኖርን ወደድኩዋት፡
ሁኜ ከየትም
በሃሳብም በስሜትም
ደግሞ ሁለት ሺዉ፡
ነፋሴ
ወንዜ
ህዝቤ
አገሬ አስባለኝ፡
እኔማ የምኖርለት አለኝ
ጤና ይስጠኝ!
እድሜ ይስጠኝ።

Back to Meskot

The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by Meskot. You may contact Amanuel Belay for comments at amanbelay3@yahoo.ca.